ከሰዓቲቱ (ቂያማ) ምልክቶች መካከል ዕውቀት ይነሳል፣ መሀይምነት ይስፋፋል፣ ዝሙት ይበረክታል፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣት ይበዛል፣ ለሀምሳ ሴቶች አንድ (ወንድ) አስተዳዳሪ እስኪሆን ድረስ ወንዶች አንሰው ሴቶች ይበዛሉ።

አነስ -አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ፦ "ከኔ ውጪ ማንም የማይነግራችሁን ከነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም
በእርሳቸው ላይ ይስፈን የሰማሁትን አንድ ሐዲሥ እነግራቹሀለሁ። የአላህ መልክተኛ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን
እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ "ከሰዓቲቱ (ቂያማ) ምልክቶች መካከል ዕውቀት ይነሳል፣ መሀይምነት ይስፋፋል፣ ዝሙት ይበረክታል፣ አስካሪ
መጠጥ መጠጣት ይበዛል፣ ለሀምሳ ሴቶች አንድ (ወንድ) አስተዳዳሪ እስኪሆን ድረስ ወንዶች አንሰው ሴቶች ይበዛሉ።"
[ሶሒሕ ነው።] [ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈን የቂያማን መቅረብ ከሚያመላክቱ ነገሮች መካከል የሸሪዐ ዕውቀት መነሳቱን ገለፁ። ይህም የሚሆነው ዑለሞች በመሞታቸው ነው። የዚህም ውጤት የመሀይምነት መሰራጨትና መብዛትን፣ የፀያፍ ድርጊቶችና ዝሙት መስፋፋትን፣ አስካሪ መጠጥ መጠጣት መብዛትን ያስከትላል። ለሀምሳ ሴቶች ጉዳይ የሚያስፈፅመውና የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማሟላት ኃላፊነት የሚወስደው አንድ ወንድ እስኪሆን ድረስ የወንዶች ቁጥር ሲመነምን የሴቶች ቁጥር ደግሞ ይጨምራል።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/65021